ይድረስሽ ለእህቴ፡ ለሜሮን ጌትነት
መታወሻ ይሁን፡ ለተወዳጇ ክብርት
ስዞር አገኘሁት፡ ግጥምሽን በድንገት
የደርሰብኝን፡ ነገርሽኝ በእዉነት

እባክሽ እህቴ፡ ግጥሙን አንብበሽ
አሰሚው ለህዝቡ፡ በሚያምረው ድምጽሽ

ሀገርከን አትልቀቅ፡ ብለሽ ጀመርሽና
ባለቅ ድርሻየን፡ ነገርሽኝ በቁና
ዘመድ አይራቅ ሲባል፡ እሰማው የነበር
እዉነትሽን ነው አሁን፡ ያንም ሁሉ ሲቀር
እናቴ ኢትዮጵያ፡ ወይ አገር ወይ አገር
አልለቅሽም አንችን፡ እሞትልሻለሁ፡ ሲባል እንዳልነበር
ልጇ ወጥቷል ሄዷል፡ በኩራት ሲነገር
ከበሮ ሲመታ፡ ከሌላ አገር ገብቷል፡ ተብሎ ሲደነከር
የስደት አመት በአል፡ በድግስ ሲከበር
ተብሏል የእድገት ዉጤት፡ በዘረኞች መንደር

ስሚኝ እኮ እህቴ፡ እንዲህ ነው ነገሩ
እያፈናቀሉ፡ ዜጎችን ቢያባሩ
ዘረኞች በቦታው፡ ቤታቸዉን ቢሰሩ
ስንዝር መቀበሪያ፡ ቢጠፋው አገሩ
መኖሪያ ነው እንጅ፡ የታጣው መንደሩ
መቀበሪያስ አለ፡ ሰሃራ በረሃ ከአሸዋው ከአፈሩ
እልፍ ከተባለም፡ ባርካው ይሰጥምና ከቀይ ባህሩ
አዲስ ነገር አይደል፡ ይኸው ነው ሚስጥሩ

የእዉቀቱንና፡ የትምህርቱን ነገር
ጆሮ ከፉ አይስማ፡ ይቅር አይነገር
ድፍን አገሪቱን ሞልቷል፡ ትምህርት ቤት
ለወጣት ማጎሪያ፡ የህጻናት በረት
መች ተነግሮ ያልቃል፡ ስለ ትምህርቱማ
ባልተማሩት ዲግሪ፡ ወረቀት ለቀማ
ማስተር ፕሮፌሰር፡ እስከ ዶክትሬት
ያበራል ቀለሙ፡ ወረቀት ሲያዩት
የተመረተዉን፡ በእነ ደደቢት
እዉቀት አይሆናቸው፡ ወስደው ቢሰቅሉት
እረ ለመሆኑ፡ አለ ወይ ትምህርት?
ካለ መጠራነፍ፡ አንድ ሰው ለአምስት
ከዛ ትምህርት ቤት፡ የሚወጣዉማ
ሳይንስ ሂሳቡም፡ ቋንቋዉም ጠማማ
ደንቆሮ ማምረቻ፡ መሆኑን ስንሰማ
እግዚኦ ያሰኛል ለአዋቂው ሰዉማ

የሶስት ወር ኮርስ ዋጋ፡ ብለሽ የተደነቅሽ
እሱማ ብዙ ነው፡ አዳምጭኝ ልንገርሽ
የኛው ባለስልጣን፡ ግድግዳው ለጥፎት
አላፊ አግዳሚዉን፡ የሚያታልልበት
በብዙ ሽህ ዶላር፡ የተከፈለበት
የሚገዛ ዲግሪ፡ አለ በኢንተርኔት
በሶስት ደቂቃ፡ ታትሞ የሚቀርብለት

አወይ ስልጣኔው፡ ወደኋላ ጎታች
ከሞቱትም በላይ፡ ከቆሙትም በታች
የራሱን አጥፍቶ፡ የሰዉን አመቻች
ቢገዙት የሚሸጥ፡ አገሩን በሞላ

እናቱ አውጥታለት፡ ስሙን የሚጠላ
ባዶ ስልጡን መሳይ፡ ልታይ ባይ ተላላ
የራሱን ማር ትቶ፡ የሌላን መርዝ በላ

ወዳጄ፡ ፖሊሱን አይተሻል? በድፍን ኢትዮጵያ
በእራሱ ቋንቋ እንኳን፡ የሌለው መጠሪያ
ሃምሳ አለቃ ቀርቶ፡ ስሙ ሳጂን አይደል?
ምስኪኑ ፖሊስም፡ ተብሏል ኮንስታብል
ቅኝ ግዝት ይሉሻል፡ ይኸው ነው ትርጉሙ
ፈረስ አስረካቢ፡ እስከነ ልጓሙ
የኛን አጥፉትና፡ የናንተዉን አልሙ
የሚል ትዉልድ መጥቷል፡ የተዛባ ትልሙ

ቋንቋዉን አጥፍቶ፡ የሰዉን ተዉሶ
ሰልጥኛለሁ ብሏል፡ ዘረኛ በስብሶ
ጥራዝ ነጠቅ ቃላት፡ ከቲቪ ያይና
ፈረንጅ ነኝ ይላል፡ ይህ ባለ ገመና
ተልኮ የመጣ፡ ቀድሞ የዘመተ
ቋንቋዉን ሊያጠፋ፡ ምሎ የተገዘተ
የፈረንጅ ቃል መጥራት፡ ሆኖት ስልጥንና
ዘነበች ምግብ ቤት፡ መባሉ ቀረና
ዴንቨር ካፌ ሆኗል፡ ተሰለጠነና
ዘረኞች ዘራርፈው፡ ድንጋይ ይከቡና
አስራ አምስት ሃያ ፎቅ፡ ሆቴል ይባልና
ድንጋዩም ተነፍጎ፡ ኢትዮጵያዊነቱ
ፍሎሪዳ ይባል ወይስ ዋሽንግተን፡ ብለው ሲሟገቱ
በቀን አቃጠሏት፡ ዜጋይቱን ጣይቱ

የአገሬ ሰዉማ፡ ለማኝ ሆኗል አሉ
ተመልካች እርሱ ነው፡ እነርሱ ሲበሉ
ትራፊያቸው እንኳን፡ ለለማኝ እንዳይደርስ
በነ ግፍ አይፈሬ፡ የድሃ እንባ ሲፈስ
ቡሌ ነው እያሉ፡ ይሸጡታል በጉርስ

ከኛ በላይ አምላክ፡ የለምም ብለዋል
በዘር ተወጥረው፡ ሃዉልትም ቀርጸዋል
እግዚአብሄርን ከደው፡ ሰይጣን ጸንሰዋል
ሃይማኖት ተናቀ፡ መቅደስ ተቀረዘ
በኢጋዚ ወታደር፡ ተረግጦ ረከሰ
ሕዝብ እንኳ እንዳይጠራው፡ ፈጣሪ ተረስቷል
እግዚአብሔር ይመስገን፡ የሚልም ሰው ጠፍቷል
ሰላም ነህ፡ ሰላም ነሽ፡ በእግዜር ተተክቷል

ያልሄድኩ እናዳይመስልሽ፡ ቀበሌም ሄጃለሁ
ከመጉላላት በቀር፡ ምንስ አግኝቻለሁ
ለግዚአብሄር ሰላምታ፡ ብል ደህና አደራችሁ
አናናግርም አሉን፡ ሸህ ብር ካልያዛችሁ
ለጆሮማ ጉድ ነው፡ አይሰማ እኮ የለው
እነቀበሌዎች፡ ሲያወሩ የሚሰማዉ
ዛሬ ስንት ሰራሽ፡ አንተስ ስንት አፈራህ፡ ሲባባሉ እኮ ነው
ስራው ምን መሰለሽ?
ህዝብን ማስተናገድ ጨርሶ እንዳይመስልሽ
ሲነጋገሩ ነው፡ ስንት ጉቦ በላህ፡ አንችስ ስንት በላሽ

አዲሱ ስልታቸው፡ ዜጋ ማሰቃያው
ግብር ሆኗል አሁን፡ ጉልበትን ማሳያው
እንጀራውን ጋግራ፡ ሽጣ እንዳትኖርበት

በአምስት ሽህ ግብር፡ ምጣድ ሲይዙባት

ልጅ እንዳታሳድግ፡ ሞትን ሲፈረዱባት

ምን አማራጭ አላት፡ በረሃብ ከመሞት?

ጸጉር ላስተካክል፡ ብለሽ ብትነሽ

ቀበሌ ይደርሳል፡ ቤትሽን ሊዘጋብሽ

እስኪ አስቢ እህቴ፡ ምንስ ታደርጊያለሽ?

ከአገር እንዳትኖሪ፡ በግልጽ ሲፈርዱብሽ

መልቀቁስ አይበዛም፡ እንዲያዉም ሲያንስብሽ

አላማቸው ያዉ ነዉ፡ አንችን አስለቅቀው ቤትሽን ሊወርሱብሽ።

gashakelemu@yahoo.com